# የACPS Express 10/28/2022: መጪው - የኖቬምበር (November) ወር ክንውን — የማህበረሰብ ተሣትፎ እና የቀን-መቁጠሪያ (Calendar)፣ ማስታወሻዎች

## መጪው - የኖቬምበር (November) ወር ክንውን: የማህበረሰብ ተሣትፎ እና የቀን-መቁጠሪያ (Calendar)፣ ማስታወሻዎች

Community Outreach

& CALENDAR REMINDERS

ለኖቬምበር (November) 2022፤ ስለ የቀን-መቁጠሪያ (Calendar) ማስታወሻዎች እና ስለ መጪዎቹ የማህበረሰብ ዝግጅቶች፤ እወቁ። የACPS የማህበረሰብ ሁሉን-የሚያዳርስ (Community Outreach) ቡድን፤ በእናንተ አጎራባች-አካባቢ - መቼ እንደሚገኙ እወቁ!

**ESL II - የመነጋገሪያ ክለብ (Conversation Club)፣ ለመካከለኛ-ደረጃ (Intermediate) 'ESL' ተናጋሪዎች**
በኖቬምበር (November) ወር ውስጥ - ዘወትር ሰኞ ቀናት፣ እና ሮብ ቀናት ላይ (ኖቬምበር/Nov. 2, 7, 9, 14,16, 21, 23, 28)፣ ከ5:30 - 6:30 p.m.
ቻርልስ ኢ. ቢትሊ (Charles E. Beatley Jr.) Central Library (5005 Duke St.). [የአሌክሳንድርያ የመጽሐፍት-ቤት (Library)]፤ የመማር፣ የመዳሰስ፣ የመፍጠር እና ግንኙነት-ማድረጊያ ዕድሎችን በመፍጠር - ማህበረሰብን ይገነባል። የ'ESL II Conversation Club'፣ ለመካከለኛ-ደረጃ ላይ ያሉ ተናጋሪዎች (intermediate speakers)፣ እንግሊዘኛ ቋንቋን ልምምድ እንዲያደርጉ እና በራስ-መተማመናቸውን እንዲገነቡ የሚያገለግል-ቦታ ነው። ምዝገባ፣ አያስፈልግም።

**የመጀመሪያ-ደረጃ & PreK-8 ኮንፈረንሶች**
ዘወትር-ሐሙስ ቀናት፤ ኖቬምበር (Nov.) 3 እና አርብ፣ ኖቬምበር (Nov.) 4
የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለቤተሰቦች እና አስተማሪዎች፣ ስለ ተማሪው የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የመማር ላይ - ስለሚያሳየው እድገት ለመወያየት፤ በጣም ጠቃሚ-የሆነ እዕድልን የሚሰጥ ነው። ስለ ኮንፈረንሶቹ የጊዜ ሰሌዳን በተመለከተ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል። (እባካችሁ አስታውሱ: ይህ - በኦክቶበር/October ወር ላይ ኮንፈረንሶቻቸውን ያካሄዱትን - የሣሙዔል ተከር (Samuel W. Tucker ) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦችን አይጨምርም።)

**የ'Día de los Muertos' ክብረ-በዓል**
ዘወትር ሐሙስ ቀናቶች፤ ኖቬምበር (Nov.) 3፣ 4 - 5 p.m.
ቻርልስ ኢ. ቢትሊ (Charles E. Beatley Jr.) Central Library (5005 Duke St.)
የአሌክሳንድርያ የመጽሐፍት-ቤት (Library)ን፣ ለ[Día de los Muertos] ክራፍትስ (crafts) አብራችሁ-ተካፈሉ፤ ወይም ለአንድ-ለምትወዱ - የማህበረሰባችን ማስቀመጫ (community altar) ፎተግራፍ ወይም የሚሰጥ-ነገርን አምጡ። ማስቀመጫው (The

altar) እና የእንቅስቃሴ ጠረጴዛው፤ ከ'reference desk' አጠቡብ የሚዘጋጅ-ይሆናል። ለማስቀመጫው (altar) የሚመጡ ዕቃዎች - ከኦክቶበር (Oct.) 28-ኖቬምበር (Nov.) 3 ቀን ድረስ፤ ቡታው-እንደፈቀደ - የምንቀበል-ይሆናል።

**የተወላጅ አሜሪካውያን የባህላዊ የዶቃ-ስራ (Native American Cultural Beading) አውደ-ጥናቶች**
ቅዳሜ፤ ኖቬምበር (Nov.) 5፣ ከ10 a.m. - 2 p.m.
እሁድ፤ ኖቬምበር (Nov.) 6፣ ከ10 a.m. - 2 p.m.
ዶ/ር ኦስዋልድ ደራንት (Dr. Oswald Durant) Memorial Center (1605 Cameron St.)
የቀረበው፤ በ'Running Strong American Indian Youth' እና የገንዘብ-እርዳታን ያገኘው - በከፊል በCity of Alexandria's Office of the Art ነው፤ እነዚህ አውደ-ጥናቶች - ለማህበረሰቡ በክራፍት/craft-ስራዎች ችሎታዎች ለመለማመድ እና ስለ ተወላጅ አሜሪካውያን የዶቃ-ስራ እና ባህል ለመማር ዕድል ይሰጣቸዋል።

**የACPS የሠራተኛ የሙያ-ማሳደጊያ ቀን (Staff Development Day**)
ማክሰኞ፣ ኖቬምበር (Nov.) 8 ቀን
ለተማሪዎች፤ ትምህርት አይኖርም።

**ALIVE! ለአጭር-ጊዜ ብቅ የሚሉ የምግብ ማከፋፈያ-ቦታዎች (Pop-Up Food Distribution)**
ሐሙስ፤ ኖቬምበር (Nov.) 10፣ ከ4:30 - 6 p.m.
ካሳ ቺሪላጉዋ/Casa Chirilagua (4109 Mt. Vernon Ave.)
ALIVE!፤ የአካባቢው ለትርፍ-የማይሰራ ድርጅት (not-for-profit organization) ሲሆን፤ በድህንነት ለሚኖሩ የተራቡ - በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ የሚገኙ - ልጆች፣ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች፣ የአስቸኳይ-ጊዜ እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን በመስጠት በትጋት የሚሠራ ነው። ALIVE! ምግብ-የያዙ ከረጢቶችን (bags)፣ ለአሌክሳንድርያ ከተማ ነዋሪዎች ያከፋፍላል። ምንም፣ መታወቂያ (ID) አያስፈልግም።

**የ'Alexandria West Community Planning Process' የማስጀመሪያ ስብሰባ**
ማክሰኞ፣ ኖቤምበር (Nov.) 15 ቀን፣ በ7 p.m.
በርቀት/Virtual (ዙም/Zoom)
የማህበረሰብ አባላቶች፣ የንግድ-ተቋማት እና ድርጅቶች በርቀት/virtual የማስጀመሪያ ስብሰው መክፈቻ በሆነው በ'City's 18-month Alexandria West planning process' ላይ እንዲካፈሉ ተጋብዘዋል። ለአካባቢው የረጅም-ጊዜ የወደፊት እቅድ ራዕይ ለመፍጠር እና በሚከተሉትን ርዕሶች ላይ - እንደ የመኖሪያ-ቤትን በተመጣጣኝ-ዋጋ ማግኘት፣ ፍትሃዊ-እኩልነት፣ ባህል፣ የመሬት አጠቃቀ፣ ከቦታ-ቦታ ዝውውር፣ የእግረኛ እና የብስክሌት-ነጂዎች የደህንነት ጥበቃ እና አገልግሎትን ማግኘት፣ እና በአሁኑ-ጊዜ ያሉትን እና የወደፊቶቹን ክፍት-ቦታዎች ማገናኘት ላይ - እርዱ። የማስተርጎም አገልግሎቶች፤ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ፣ የሚቀርብ-ይሆናል።

**The LINKS, Inc. - Arlington Chapter S.T.E.(A).M. Pathways to A Lifetime of Unlimited Success (P.L.U.S.) ሴሚናሮች (Seminars)**
ቅዳሜ፤ ኖቬምበር (Nov.) 19 እና ቅዳሜ፣ ዲሴምበር (Dec.) 3
Charles Houston Recreation Center (901 Wythe St.)
የአሌክሳንድርያ እና የአርሊንግተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ ለ'STEAM PLUS ሴሚናሮች/seminars፣ እንዲመዘገቡ ተጋብዘዋል፤ ይህን በእጅ-ሊሰሩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን እና ብሩህ-አዕምሮ ያላቸው (dynamic) ተጋባዥ ተናጋሪዎችን - በተለያዩ የ S.T.E.A.M. ሙያዎች ላይ ቀለም-ያላቸው (color) በተገቢው-ሁኔታ ያልተወከሉትን - ታዳጊ ሴቶች እና ወንዶች - በማስተዋወቅ የሚያንጸባርቅ-ነው። 'The Links, Inc.'፤ የሃገሪቱ ረጅም-ዕድሜ ያለው እና ትልቁ የበጎ-ፈቃድ ስራ አገልግሎት አንዱ-ሲሆን፤ ከአፍሪካ-የመጡ ሴቶች ባለሞያተኞችን ያይዘ ነው።

**ALIVE! ለአጭር-ጊዜ ብቅ የሚሉ የምግብ ማከፋፈያ-ቦታዎች (Pop-Up Food Distribution)**
ቅዳሜ፤ ኖቬምበር (Nov.) 19 ቀን፣ ከ8:30 - 10:30 a.m.
ኮራ ኬሉ (Cora Kelly) የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት (3600 Commonwealth Ave.)

ALIVE!፤ የአካባቢው ለትርፍ-የማይሰራ ድርጅት (not-for-profit organization) ሲሆን፤ በድህንነት ለሚኖሩ የተራቡ - በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ የሚገኙ - ልጆች፣ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች፣ የአስቸኳይ-ጊዜ እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን በመስጠት በትጋት የሚሠራ ነው። ALIVE! ምግብ-የያዙ ከረጢቶችን (bags)፣ ለአሌክሳንድርያ ከተማ ነዋሪዎች ያከፋፍላል። ምንም፣ መታወቂያ (ID) አያስፈልግም።

**ACPS የበልግ የዕረፍት-ጊዜ (Fall Break)**

ከሮብ፣ ኖቬምበር (Nov.) 23 እስከ አርብ፣ ኖቬምበር (Nov.) 25 ቀን ድረስ

ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች፣ ለበልግ የዕረፍት-ጊዜ (fall break) ዝግ-ይሆናሉ።

## ‘SEAL’ በስራ-ላይ ሲውል: ጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት




ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) - ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች፤ ግልጽ-ሆነ ምን እንደሚሰማቸው ለመናገር — እራሳቸውን ለመግለጽ ረድቷቸዋል። ስለ ‘SEAL’ ልዩ የሚያደረግው ሁኔታ፤ ስለተፈጠረው ነገር እውነተኛነታቸውን ጠብቀው-በሚገኙበት ሁኔት፤ ለሁሉም የዕድሜ ቡድን ላሉ ተማሪዎች እንዲስማማ-ሆኖ መዘጋጀቱ ነው። ንብኙ-የሆኑት የጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት አስተማሪ - የ‘ሺአኢና ታመስ (Shaina Thomas)’ የስምንተኛ ክፍል ስለ ‘SEAL’ ያለውን እይታ ለመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች በስራ-ላይ ሲውል አሳይተዋል።




ተማሪዎች በግማሽ ክብ ቅርጽ ባለው የወንበር-አቀማመጥ የተቀመጡ፣ እና ሁሉም ዓይኖች - ‘SEAL Time’ ተብሎ ከፊት-ለፊት ስክሪን (screen) ላይ በተፃፈው ላይ ትኩረት አድርገው-ይቀመጣሉ። የዕለቱ ጥቅስ ከኢንተርፕሩነር ጂም ሮህን (entrepreneur Jim Rohn) የሚከተለውን ከተናገሩት- በመቀጠል-ይመጣል - “የዕድገት-ሂደትን፣ ካለ ውሳኔዎች ማግኘት አይቻልም/You cannot make progress without making decisions”። የቀኑ - ‘ቃል’ ደግሞ፤ “የማገናዘብ-ጥበብ/discernment” ነው። ጥቅሱ፣ ውይይት መጀመሪያ ሆኖ፤ ታመስ (Thomas)፣ የ‘discernment’ ትርጉም ምን እንደሆነ ክፍሏን ትጠይቃለች። አንድ ተማሪ ሲመልስ፤ “ነገሮችን፣ እንዴት በሚገባ መረዳት” ማለት ነው ብሎ መልሷል። ታመስ (Thomas) የበለጠ ሲያስረዱ፤ የ‘discernment’ - በውሳኔ-አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚገባ እና አንድን-ሰው በምርጫቸው ላይ ሊሰርስ-የሚችለውን ነገር ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ይረዳል።

ቪዲዮ መታየት-የጀመረ እና፣ ታሪኩም ስለ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ስለሆነች እና ስሟ አማንዳ ስለተባለች፤ በእቃ-መቆለፊያና ማስቀመዳ ክፍል (locker room) ውስጥ፣ በሁለት የስምንተኛ-ክፍል ተማሪዎች - አንድ ሌላ ተማሪ ላይ ስያላግጡባት ስለማየታ የሚያሳይ-ነው። ታመስ (Thomas)፤ ለክፍሏ፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ-ምን ሊያደርጉ ይችሉ እንደነበር - ጥያቄ ጠይቃለች። አንዳንድ-ተማሪዎች፤ ሁኔታውን በቪዲዮ እንደሚቀርጹ ሲመልሱ፤ ሌሎች ደግሞ እርዳታ-እንደሚፈልጉ፣ ወይም ዝም-ብለው ትተው-እንደሚሄዱ ተናግረዋል።



አስተማሪው፤ ነገሩን አንድ-እርምጃ ወደፊት ወስደው፣ የግላቸው-እንዲሆን አደረጉት። ለተማሪዎቿ የጠየቀቻው፤ ስሜታቸውን ለሚጓደው ጓደኛደው - አንድ ሰው ሊወስድ የሚችለው ተግባራዊ-የሆነ ውሳኔ ምንድነው፣ የሚል ጥያቄ አቀረበችላቸው። አሁን፤ በዙሪያው የመቀባበያ ጊዜ ነው “በእጅ ትንሽ-ዕቃን መያዝ/the talking piece” - ድንጋይ (rock)፤ ተማሪዎች በሚይዙት ጊዜ፤ ስሜታቸውን ለመግለጽ የእነርሱ-ጊዜ እንደሆነ የሚያሳይ-ነው። ሊደርስ-ስለሚችለው ሁኔታ አስተማሪያቸው ያቀረቡላቸው ላይ ከግምት-ውስጥ በማስገባት፤ አንድ ተማሪ - “በቡጢ ማለት-ነው/smack them” ላለው - ታመስ (Thomas) ለማስታወስ-የተናገሩት፤ በዚህ-ሁኔታ ውስጥ፣ የሚወስዱት እርምጃ ምን የሚያስከፍላቸው-ነገር አብሮ እንደሚመጣ ከግምት-ውስጥ ማስገባት ያለባቸው እንደሆነ፣ በርግምጥ ይህ ችግር-ውስጥ የሚከት መሆኑን ተናግረዋል። ሌሎች ተማሪዎች ሲመልሱ፤ “ለአንድ-ሰው መናገር/tell somebody”፣ “ዞር ብሎ መሄድ/walk away”፣ ‘ምን ዓይነት ስሜት እየፈጠሩ እንደሆነ መናገር/express how they make you feel”፣ ወይም “ምንም ነገር አለማድረግ/don’t do anything at all” የሚሉም-ነበሩበት።

ወደ ተማሪዎቿ ሁሉን-ለማኘት ማዳረስ፤ ታመስ (Thomas) ለማስታወስ-ያህል የተናገረችው፤ በጥብቅ-ጓደኝነቶች ውስጥ - የስሜታዊነት የደህንነት-ጥበቃ ኖሯችሁ፣ ምን እንደሚሰማችሁ ለመወያየት እና ጓደኞችም-ይህን ስሜታችሁን ሊያከብሩ-ይገባል፤ ብለዋል። ተማሪዎች ይህን ተጨማሪ ይህን አዲስ-የሆነ የሕይወት የአኗኗር ችሎታ ብቃትን - በውሳኔ-አሰጣጥ ሂደት፣ ወደ ጥሩ ምርጫዎችን ወደማድረግ የሚመራ፤ ትምህርትን አግኝተዋል።

ከSEAL ተማሪዎች ምን እንደተማሩ - ታመስ (Thomas) ለተጠየቀችው-ጥያቄ፣ ፈጣን ምላሽ ስትሰጥ፤ “እርስ-ራሳቸው ቢሆኑ የማይነጋገሩበትን፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የመወያያ ቦታ እንዲኖራቸው አድርጓል” ብለዋል። ታመስ (Thomas) ሲገልጹ፤ ‘SEAL’፣ ተማሪዎች እራሳቸውን ለመግለጽ እንዲናገሩ ያደረጋቸው፣ እና ይህም የቀለም-ትምህርት ሂደታቸው ላይ በአዎንታዊ-ሁኔታ አስተዋፅዖ ያበረከተ ነው። “SEAL - ተማሪዎች የበለጠ ወደውስጥ-እንዲመለከቱ እና ስላአላቸው የተወሰኑ ስሜቶች ተቀባይነት-እንዲኖራቸው አድርጓል፣” ብላለች። ታመስ (Thomas) በመጨመርም፤ ተማሪዎች እራሳቸውን መግለፃቸው፣ ወደ የቀለም-ትምህርቶቻቸ የሚተላለፍ በመሆኑ፤ እንደ ጽሁፍ የክፍል-ስራዎች ወይም ስነጽሁፍን እንዴት ሊመለከቱት በሙችሉበት ሁኔታ-ላይ ተያይዞ ሊያስተምራቸው የሚችል ይሆናል። የራሳቸውን በራስ-መተማመንን ለመገንባት የሚረዳ ሲሆን፤ የክፍል-ስራዎችን በመስራት ብቻ ሣይሆን፣ ነገር ግን አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎችን የመወጫ መንገዶችንም በመፈለግ ይረዳል።

ስለ ‘SEAL’ ተማሪዎች ምን እንደተሰማቸው በመለካት-ጥረት ላይ፤ ታመስ (Thomas) - ስለ ምን መወያየት እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ጥሪ-አድርጋለች። ተማሪዎች ሊያዩት የሚፈልጉት ነገር ብለው የተናገሩት፤ አሁን በ‘SEAL’ ትምህርት በሆነው ውስጥ-ለ30 ደቂቃዎች በየቀኑ በሚሰጠው ውስጥ፣ ተካክቶ የሚገኝ መሆኑን፣ ተናግራለች።

# ከመጀመሪያ-ደረጃ እና ከPreK-8 ትምህርት ቤት - የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች ሊገኙ-የሚችሉ ምርጥ-ነገሮች




የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፤ በተማሪው የትምህርት ቤት ሕይወት እና በመኖሪያ-ቤት ሕይወቱ መካከል ያለውን አስፈላጊ-የሆኑ ግንኙነቶችን የሚፈጥር-ነው። ACPS፤ የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶችን፣ በየ-የትምህርት ዓመቱ የቀን-መቁጠሪያ ሁለት ጊዜ በማካሄድ፣ ቤተሰቦች እና አስተማሪች - ስለተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የእድገት-ሂደት ላይ ለመወያየት ዕድሎችን ይሰጣቸዋል።

ለ2022-23 የትምህርት ዓመት፣ የበልግ (fall) የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለመጀመሪያ-ደረጃ እና ከPreK-8 ቤተሰቦች - በኖቬምበር (Nov) 3 ቀን 2022 እና በኖቬምበር (Nov) 4 ቀን 2022 ላይ ይካሄዳል። ስለ ኮንፈረንሶቹ የጊዜ ሰሌዳ እና ተያያዥ-የሆኑ ሎጂስቲኮችን በተመለከተ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል። ይህ - በኦክቶበር/October ወር ላይ ኮንፈረንሶቻቸውን ያካሄዱትን - የሣሙዔል ተከር (Samuel W. Tucker ) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦችን አይጨምርም። የበልግ (Fall) የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች - በሴፕቴምበር (September) ወር ውስጥ ተካሂዶ-ነበር።

ከወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ የበለጠ-ተጠቃሚ ለመሆን፤ የACPS፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ (Family and Community Engagement (FACE)፤ የሚከተሉትን በምክር-መልክ ያቀርባል:

- **ዝግጁ-ሁኑ:** አብዛኛዎቹ የACPS ትምህርት ቤቶች፤ የ'ParentSquare' የጊዜ-ሰሌዳ የኮንፈረንስ ጊዜያቶችን ለቤተሰቦች ይጠቀማል። ቀልጣፋ እና ቀላል የምዝገባ ሂደት መኖሩን ለማረጋገጥ፤ በ'ParentSquare' አካውንታችሁ መመዝገባችሁን አረጋግጡ፣ እና አፕ (app) ዳውንሎድ ማድረግዎን እርግጠኛ ሁኑ።
- **ሁሉንም ሰው በአንድ-ገጽ ላይ እንዲመጣ-አድርጉ:** ልጅዎ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ እና የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪ ካለው/ላት፤ ሁለቱም በኮንፈረሱ ውስጥ እንዲገኙና የተማሪዎ የእርዳታ ቡድን ግንኙነት እንዲያደርጉ መጠየቅ-ትችላላችሁ።
- **ጥያቄዎችን ጠይቁ:** የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - በአጠቃላይ ከ10-15 ደቂቃዎችን ይወስዳል። ከስብሰባው አስቀድማችሁ፣ ለአስተማሪው ማቅረብ የምትፈልጓቸውን ጥያቄዎች ዝርዝር አውጡ። አስፈላጊ-ከሆነ፣ በማንኛውም ጊዜ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ ለመጠየቅ አትፍሩ።
- **ማስታወሻዎችን ውሰዱ:** በኮንፈረንሱ ጊዜ፤ ቀናቶችን ፃፉ፣ የተጋሩ-ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እና የአስተማሪው ለጥያቄዎ-ሰጡትን መልስ ፃፉት።
- **ልጅዎን ያሳትፉ — ከስብሰባው - በፊት እና በኋላ:** አስቀድመው - ከልጅዎ ጋር ተነጋገሩበት፤ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ የሚወዱት የትምህርት-ዓይነት እና እንቅስቃሴ ምን እንደሆነ ጠይቁ፤ እንዲሁም፣ የማይወዱትስ ምንድነው፣ ለምን - ብላችሁ ጠይቁ። ከዚያ-በኋላም፤ ምን እንደተማራችሁ እና ከትምህርት ቤት ጋር ልጅዎን ወደ ስኬት እንዲደርስ ለመርዳት ምን-እንደምታቅዱ አጋሩ።

ብዙ የACPS ቤተሰቦች፤ በ'ParentSquare' ድህረ-ገጽ፣ በኢሜል ማገናኛ (email link፣ በቴክስት ማገናኛ (text link) ወይም በአፕ (app) ማስታወቂያዎች - አማካኝነት ወደ ኮንፈረንሶቹ ለመመዝገብ (sign up) ለማድረግ የሚችሉ-ይሆናል። እባክዎን፤ እነዚህን ደረጃ-በደረጃ የሚወሰዱ መመሪያዎችን አመላክቱ: በEnglish (PDF) | en español (PDF) | አማርኛ (PDF) | بالعربية (PDF)

## ከPTAC፣ PSAS እና የACPS የሕዝብ የደህንነት-ጥበቃ ፎረም፣ የተቀረጹ-ቅጂዎች (Recording) - ይገኛሉ




የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (The Alexandria PTA Council (PTAC)፤ ወላጆች ደህንነቱ-ለተጠበቀ የአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤት (Parents for Safe Alexandria Schools (PSAS)፣ እና የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ የሕዝብ የደህንነት-ጥበቃ ፎረምን - በኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን 2022 ላይ አዘጋጅቷል። የዝግጅቱ የተቀረጹ-ቅጂዎች (Recordings) - በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ እና በአረብኛ [በዝግጅቱ ድህረ-ገጽ ላይ መገኘት-ይቻሉ]።

ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፣ እና የፓኔል ኤክስፐርቶች፤ በትምህርት ቤቶቻችን እና በማህበረሰባችን ውስጥ፣ የደህንነት-ጥበቃን ጠብቆ-በመገኘት ላይ - የክፍሉ/divisionን - ከአሌክሳንድርያ ፖሊስ መምሪያ (Alexandria Police Department (APD) ጋር የሚያደርገውን ትብብር፣ እና በዚህ የጋራ-በሆነ ዓላማ ላይ ቤተሰቦች - ከACPS-ጋር እንዴት እንደሚሠሩ፤ ተናግረዋል። ፓናሊስቶች ሆነው የተካተቱት:

- የACPS የደህንነት እና የጥበቃ አገልግሎቶች (Safety & Security Services) ዳይሬክተር — ጆን ኬንትሬራስ (John Contreras)።
- የACPS የትምህርት ቤት የማህበራዊ ስራ ዳይሬክተር — ፋይዛ ጃክሰን (Faiza Jackson)።
- የአሌክሳንድሪያ የፖሊስ መምሪያ ሹም — ሪቻርድ ሳንዳቮል (Richard Sandavol)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ የወንበዴ-ቡድን (Gang) መከላከያ የማህበረሰብ ታስክ-ፎርስ (Task Force) አባል — ማይክ ማኪይ (Mike Mackey)።
- የ'Be SMART' የጦር-መሣሪያ (Gun) በጥብቅ-ቦታ ማስቀመጥ (Secure Gun Storage) ፕሮግራም፤ የእያንዳዱ-ከተማ የጦር-መሣሪያ (Gun) የደህንነት-ጥበቃ — አንዲ ኮርሶ (Andy Corso)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ፣ የመጓጓዣመምሪያ (Department of Transportation) & የአካባቢያዊ አገልግሎቶች (Environmental Services) — አሌክስ ካሮል (Alex Carroll)።

## ለመዋዕለሕፃናት የእድገት ሂደት ሪፖርት እና ከ1-5 የመጀመሪያ-ደረጃ የእድገት ሂደት ሪፖርት - ለንባብ ክፍለጊዜዎች የተደረገ-አዲስና ማሻሻያ (Update)



የንባብ የችሎታ-ብቃትን በተስፋፋ የመመደቢያ ክፍሎች ውስጥ ከመመደብ ይልቅ፤ እንደ ‘Above Level’፣ ‘On Grade Level’፣ ወይም ‘Below Grade Level’፤ ከማለት ይልቅ፤ የንባብ መደበኛ-ደረጃ (reading standards) በ2022-23 ከ1-5 ክፍሎች - የመጀመሪያ ደረጃ የእድገት ሂደት ሪፖርት ላይ - ስለተማሪያቸው የችሎታ-ብቃት በተወሰነ ይዘቶች በሆነ በንባብ ሂደት ውስጥ - ከሚገልጽ መረጃ ጋር ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች የሚሰጥ-ይሆናል። በተመሣሣይ ሁኔታ፤ ለመዋዕለሕፃናት የዕድገት ሂደት ሪፖርት - አምስቱ መደበኛ ደረጃዎች (standards)፤ ወሳኝ-የሆነው የንባብ ችሎታዎችን መሠረታዊነትን ሊይናጸባርቁ በሚችሉት - በሁለት መደበኛ ደረጃዎች (standards) እንዲካተቱ ተደርጓል። እነዚህ ለውጦች፤ ከሌላ የይዘት አካባቢዎች ውስጥ በጥቅም-ላይ ከሚውለው የዕድገት-ሂደት ሪፖርት ጋር ተመሳሳይነት እንዲኖረው በማድረግ፣ የተማሪውን የችሎታ ብቃትን ከክፍል-ደረጃ መደበኛዎች ጋር ግንኙነት-እንዲኖራቸው የሚያገለግል መሣሪያ ሆኖ ጥቅም-ላይ ይውላል።

ከእነዚህ ማሽጋሸጊያዎች ጋር፤ እንክብካቤ-ሰጪዎች እና ትምህርት-ሰጪዎች - በትምህርት አሰጣጡ እና በክፍል-ስራ ላይ በከፍተኛ-ደረጃ የችሎታዎች መመዘኛ ላይ ትኩረት በማድረግ - የተማሪዎችን የንባብ ስኬት ለማሳደግ ይሰራሉ። ስለእነዚህ ለውጦች - ተጨማሪ መረጃዎች፣ በ‘Progress Report FAQ’ ገጽ በሆነ የACPS ‘Growing Readers Literacy Family Resource’ በካንቫስ ገጽ (Canvas Site) ላይ፤ መገኘት-ይችላል። ስለ ንባብ የእድገት-ሂደታቸው ካሏችሁ ጥያቄዎች ጋር - እባካችሁ የልጅዎን አስተማሪ አነጋግሩ፤ እና የመረጃ-ምንጮችን ለመፈለግ እና የማንበብና መፃፍ ዕድገት ላይ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ለመርዳት-እንድትችሉ፤ በACPS ውስጥ፣ ‘Growing Readers & Writers’ን ጎብኙ!

ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ የACPS የመጀመሪያ ደረጃ የስነጽሁፍ (Literacy) የትምህርት አሰጣጥ ባለሞያ የሆኑትን - ዶ/ር ካሮሊን ውስተር (Dr. Carolyn Wooster)ን በcarolyn.wooster@acps.k12.va.us አነጋግሩ።

## ለኖቬምበር (Nov.) 10 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



የሚቀጥለው መደበኛ የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘለት፣ ለኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 ነው። ለዚህ ስብሰባ ከተዘጋጁት የአጀንዳ ነጥቦቹ መካከል - የሚከተሉት ይገኙበታል:

- የ2022-23 የ'Vision Integrity & Passion (VIP)' ሽልማቶች - የመጀመሪያ-ተቀባዮችን ዕውቅና-መስጠት።
- የአባልነት እና የመሸጋገር ሪፖርት።
- በማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) ላይ አዲስና-ማሻሻያ (Update)።
- የFY 2024-2033 የ'CIP' በጀት አቀራረብ (Presentation)።
- የጥናቶች ፕሮግራም።
- የACPS/APD MOU ማራዘሚያ (extension)።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 70.88 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።